ወያኔ እስከ መቸ ገድሎን፥ አሸብሮንና አስፈራርቶን ይገዛናል?

በሸፋን ስሙ ኢሕአዴግ ተብዮው ወያኔ/ሕወሐት ዕድሜውን ለማራዘም ይመቸው ዘንድ በውስጣችን ቅራኔን በማስፋት በዘር እያደራጀ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ሕዝብን በእሥራት፥ በግድያ፥ በበሽታና በረሐብ እየፈጀና እያስፈጀ ፋሽስታዊ ሥርዓቱን ከጫነብን ሐያ ዓመት ሊሆነን ትንሽ ቀረን። የተቃዋሚው ጎራም በረቡና ባልረቡ ልዩነቶች እርስ በርስ ባለመግባባቱና ተለጣፊውም በዝቶ ትግላችን ግብና ዓላማውን ከመሳቱም አልፎ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ አስፈራርቶና አሸብሮ ለመግዛት በሚያደርገው ትግል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ድጋፍ እያበረከተ ነው።

ድክመቶችን መጠቆሙ 'ብዬ ነበር' ለማለትና አንዳችን በሌላው ጣት ለመጠንቆልና ለማስጠንቆል ወይም ቅራኔዎችን እያሰፉ የሚመለከቱን ጉዳዮች ጭራሽ ላለማውሳት፥ ወይም በፖለቲካ ለመወንጀልና ለማስወንጀል ሳይሆን እንደ ሰለጠነ ዜጋ በችግራችን ዙሪያ መደራደርና መወያዬት ይቻል ይሆን በማለት ነው። ከብዙ በጥቂቱ ......

1ኛ/ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ያለጋራ ተሳትፎ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ችግሮች በአንድ ፓርቲ፥ ግንባር፥ ወይም ንቅናቄ የትግል ስልት ብቻ መፍታት የማይቻል በመሆኑ ወደ አንድ ገበታ ያለመምጣት፣

2ኛ/ ድርጅቶች ለፖለቲካዊ ችግሮቻችን መፍትሔ በሚሆኑ ሐሳቦችን መቀበልና መስጠት ያለመቻል፥

3ኛ/ በዋነኛነትና በመለስተኛነት መምጣትና መፈታት ያሉበትን ችግሮች ቅደም ተከተልን በተመለከተ፤ ለምሳሌም ዋነኛው የኢትዮጵያ ጠላት ወያኔ በመሆኑ በቅድሚያ ትግሉ ኢላማ ማለም ያለበት በወያኔ ላይ ሲሆን እርስ በርስ መጠላለፉንና መደናቆሩ፣

4ኛ/ በጋራ የመሥራት ተለምዶ ማጣት፥

5ኛ/ በፓርቲዎች ኅብረት የሥልጣን ጥማትና ያለመተማመን፥

6ኛ/ ለአንድ ፓርቲ የዴሞክራሲ መሰረቱ የጎሳ ነጻነት ሳይሆን የግለሰብ ነፃነት መሆኑን መርሕ አድርጎ ያለመቀበል፤ ለምሳሌ አማራ፥ ኦርሞ፥ ትግራይ... ወዘተ እያሉ በዘር ከማደራጀት ኅብረብሔራዊ ይዘትን ያለመሻት፥

7ኛ/ ከወያኔ በተወረሰው መጥፎ ፈሊጥ የዘር ፓርቲ፥ ግንባር ወይም የጎሳ ነፃ አውጪ ነኝ ባይነት ከማን ለማን? ወዴትስ ይወስደናል ብሎ እራስን ያለመጠየቅ፥

8ኛ/ ተቃዋሚ መስለው ለሥልጣን ኢትዮጵያን ለወያኔ የሸጡ እንደ ልደቱና ኃይሉ ሻውል ለመሳሰሉ ተለጣፊዎች መሣሪያ መሆን፣

9ኛ/ በግለሰብ ደረጃ ሳይማር ፖለቲካ አዋቂ ነኝ ባይነትና ከተማረው መማርን ያለመቻል፥

10ኛ/ ጎሰኝነት ከኢትዮጵያዊነት እንደ ማይበልጥና ካጠበቅነው የማያቀራርበን አጥር መሆኑን ያለመረዳት።

በስደት በሰው አገር ብንኖርም በመወለድ በእትብታችን ከአፈሯ የተቀላቀልንና በአስተሳሰብ ሆነ በሥነልቦናዊ አመለካከት ልንደብቀው የማንችለው ኢትዮጵያዊነት ከደማችን እንዳለ ግንባራችን ይመሰክራል። የአገራችን ፖለቲካ ሁላችንንም ስለሚመለከተን የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሩ ችግራችን፥ ደስታው ደስታችን በመሆኑ ዛሬ በአደጋ ላይ ላለው ወገኖቻችን ደራሽ እኛው ብቻ በመሆናችን ወያኔን የሚቃወሙ ድርጅቶች ሁሉ አንዱን ከአንዱ ሳንለይ በሞራል በጉልበት ሆነ በገንዘብ መርዳት "ኢትዮጵያን አድን" አደራና ግዴታ መሆን አለበት። በተገኘውና በተቻለው መንገድ ወያኔን ማጋለጥ፥ መቃወምና መታገል የቻለ ሁሉ ወዳጃችን ነው። በተቃዋሚው መሐል የሚፈጠሩ ጥቃቅን ልዩነቶች እንደ ዋነኛ ምክንያት ሆነው መታየት የለባቸውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር በትከሻችን ላይ በመሆኑ ሁላችንም በጥፋትዋ ላይ ዝምታ በታሪክ ያስጠይቀናል። አባቶቻችን መስዋዕትነትን ሳይከፍሉ አገራችን እንዳልቆየች ሁሉ ዛሬ ከማናችንም እንደችሎታችንና እንደየአቅማችን ይጠበቅብናል።

የወያኔ ፖለቲካዊ መጨቆኛና የአንድ ጎሳ ቅኝ አገዛዝ መሳሪያ የሆነው የአዲስ አበበው ኢጋቾ ፍርድ ቤት በቅርቡ በዋለው ችሎት በስመ አሸባሪነት ሞትና የዕድሜ ልክ እሥራት በንጹሐን ኢትዮጵያውያን ላይ መፈረጁ የፖለቲካ ቲያትር ከመሆኑም አልፎ የምርጫ ጦርነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መከፈቱን በግልፅ እያሳየ ነው። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በወያኔ/ሕወሐት እስር ቤት ናቸው። በወያኔ መንግሥት ስብዕና ክብርና ቦታ የሌለው በመሆኑ እነ ብርቱካን ሚዴቅሳና ሌሎች የሕሊና እስረኞች ወያኔ ለፈጠረው ፖለቲካዊ ችግሮች መስዋዕትነትን እየከፈሉ ናቸው።

የትግራይ ሕዝብ ትናንት የኢትዮጵያ ታሪክ ግንባታ ማዕከል እንደ ነበርክ ሁሉ ዛሬ አንድነታችን ለማፍረስ በአንተ ስም በሚነግዱ በወያኔ የተጫረው እሳት እየፈጀን በመሆኑ ከኢትዮጵያ ወገኖችህ ጎን በመቆም በነመለስ መንግሥት ላይ ክንድ በማንሳት አንድነታችን ለማስጠበቅ ቅድመ ግደታህን መወጣት በጥብቅ ይፈለግብሃል። ወያኔ ከደደቢት ተራራ ሥር ተነስቶ በአዲስ አበባ በመንገሥ በአባቶቻችን መስዋዕትነት ተከብሮ የቆየውን ድንበራችንን በማፍረስ መሬታችንን ለባዕድ በመስጠት ያደረሰብን በደል ጣሊያን ከአውሮፓ በመምጣት በቃጣብን ወረራ ካደረሰብን ጉዳት በልጦ ይገኛል። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዕራብ እያለቀ ከውጭ አገር የመጣውን የዕርዳት እህል ለማግኘት የወያኔ ደጋፊ መሆን አለበት የሚል ፖሊሲ የሚያራምድ መንግሥት ነው።

የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ ተለጣፊ የወያኔ ሥርዓት አራማጆችና ጉርሻ ተቋዳሾች ከወያኔ እኩይ ተግባር በመላቀቅ ከራሳችሁ ጥቅም የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም በማስቀደም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ከታሪክ ግድፈት እጃችሁን አጽዱ እንላለን።

የወያኔ ሥርዓት ኢትዮጵያዊነትን በጎሳ ሸንሽነህ፥ የአጥፍተህና ከፋፍለህ ግዛ በመሆኑ በተለይም አንድነታችን ከሚያናጉ በርካታ ፈርጆች ጥቂቶቹ በሐይማኖትና በድንበር መሬት ግጭቶችን መፍጠርና ደም ማቃባትና የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለባዕድ መስጠት፥ ዜጎችን ማሰር፥ መግደልና ማፈን ዋነኛዎቹ ናቸው።

በቅርቡ በኮፐንሐገን በተደረገው የዓለም አየር መናወጥን የተመለከተ በዓለም አቀፍ ስብሰባ አቶ መለስ የአፍሪካ መሪዎችን በመወከል የተላከበትን ዓላማ በመጠምዘዝ ለምዕራባውያን በመሸጥ የአፍሪካ መሪዎች ያልተስማሙበትንና ያላመኑበትን ውል ፈርሞ ተመልሷል። ከሐዲነቱንና ቅጥፈቱን በግልጽም አስመስክሯል። ይህ ድርጊቱ ኢትዮጵያ የዓለም ሰላምና የአፍሪቃ ነፃነት ሻምፒዮን በመሆን ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስከ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሥርዓቶች ከዝንባጉዌ እስከ ሳውዝ አፍሪካ ነፃነት የከፈለችውን መስዋዕትነት ከማጉደፉም አልፎ በአፍሪቃውያን ዘንድ እምነት አጉዳይ አድርጎናል፤ አሳፍሮናል፤ አዋርዶናልም። ይህ አጋጣሚ የአፍሪካ አንድነት ጽ/ቤት በአዲስ አበባ የመኖሩንና ቀጣይነቱን ኀልውና ሊፈታተን ይችላል። በተለይም የኀብረቱ ጽ/ቤት ከአዲስ አበባ ለማስነሳት ለሚቀናቀነን የሊቢያው መሪ ኮ/ል ጋዳፊ ጥሩ ምክንያት ይፈጥራል።

አንድ ጀግና አባት የአገር ምንነትን እንዲህ ይላሉ .. አገር በታሪክ በቋንቋ በሃይማኖት በልማድ በተስፋ በደስታና በመከራ ተሳስሮ የሚኖር አንድ ወገን የሆነ ሕዝብ የሚኖርበት የዓለም ክፍል ነው። አገር ማለት፤ አያት ቅድመ አያት የተወለዱበት፤ አድገው በጀግንነት ከውጭ ጠላት እየተከላከሉ፥ ለሕዝብና ለመንግሥት የሚጠቅም ሥራ ሠርተው ዕድሜያቸው ሲደርስ ልጆቻቸውን ተክተው የተቀበሩበት ጉድጓድ ነው። በመወለድ እትብት፤ በመሞት አካል ከአፈሩ ጋር ስለሚዋሐድ፤ የአገሩ አፈር ሕዝቡ በላዩ የሚኖርበት ማለት ነው። እግዚአብሔር ከምድሯ ፍሬ ሕይወት እንዲገኝባት በማድረጉ አገር እያጠባች የምታሳድግ ፍቅርዋ በአጥንትና በሥጋ ገብቶ የማይደመሰስ የሆነች እናት ማለት ነው። ከልጅነት ጀምሮ ወንዙ ተራራው ሜዳው ቆላውንና ደጋውን በማየት ስላደግን አባቶች በሕይወትና በሞት የሠሩበት ደግ ሥራ በአእምሮ ታትሞ ስለ ቀረ በአገር እስካሉ ሲታይ በስደት ሲሆን ሲታሰብ ፍቅርና ናፍቆት የሚያሳድር አገር ነው። አገር አባት እናት ዘመድ ምግብ ጌጥና ሀብት በመሆኑ ድህነትና ጥቃት በመጣ ቁጥር እስከ ሞት ድረስ እንዲሠራበት ከአያት ከቅድመአያትና ከአባቶች በጥብቅ የተሰጠ ያደራ ገንዘብ ነው። ይላሉ።

በአገራን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማምጣት በወያኔ በሩ የተዘጋ በመሆኑ፤ ማናችንም በሰላማዊ መንገድ ሆነ በአመጽ በሩን ለማስከፈት የመረጥነው መንገድ እንደምክንያት ሆኖ ሳያከፋፍለን ወያኔም ይህንን ምርጫችን ምክንያትም አድርጎ በቅራኔው ላይ ሳያካብት፤ ነቅተንና አውቀን፤ ከእነሱ በልጠን መገኘት አለብን። የዛሬው ነጥሎ ውድ የኢትዮጵያ ልጆችን በሞትና በእድሜ ልክ እሥራት ወያኔ መፈረጁ ነግ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ዕጣ በመሆኑ በተቻለን አቅም ወያኔን ለማጋለጥና፥ ትግሉን በሁሉም መስክ ለማፋፋም ቅድሚያ መስጠት አለብን። ምክንያቱም የወያኔ መንግሥት የአሸባሪዎች፣ የአፋኞች፣ የገዳዮች፣ የአፈ ጮሌዎችና የተራ አጭበርባሪዎች መንግሥት ነውና።

ሞት ለወያኔ ነፃነት ለኢትዮጵያ
ከደመላሽ ካሳ
ካሊፎርኒያ